# መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት
## አቅራቢዎች

# ደህና ሰንብት ፈርዖን!




ጸሐፊው: Edward Hughes
ምሣሌ አቅራቢው: Janie Forest; Alastair Paterson
ያሻሸለው (አሻሽሎ የጻፈው): Lyn Doerksen
የተተረጎመው: Abel Eshetu



አዘጋጁ: Bible for Children
www.M1914.org

BFC
PO Box 3
Winnipeg, MB R3C 2G1
Canada



©2021 Bible for Children, Inc.
ፈቃድ፡- ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።






ፈርዖን በጣም ተቆጣ! ባሪያ ያደረጋቸውን እስራኤላውያንን እንዲለቃቸው እግዚአብሔር በሙሴ በኩል አዝዞት ነበር፤ ፈርዖን ግን እምቢ አለ።


ፈርዖን አስገባሪዎቹን
“ስራ እያበዛችሁ
እስራኤላውያንን
አስጨንቋቸው።”
አላቸው። ስለሆነም
ኑሮ ለእስራኤላውያን
እጅግ ከፋባቸው።
3


ፈርዖንም “ሂዱ፥ ሥሩ ገለባ አይሰጡአችሁም፥ የሚፈለግባችሁን
የጡቡን ቍጥር ግን ታመጣላችሁ አላቸው።” ትዕዛዙም ጠንካራ
ነበር።
4


የፈርዖንም አስገባሪዎች፡-
ቀድሞ ታደርጉ እንደ ነበራችሁ
ትናንትናና ዛሬ የተመደበላችሁን
ጡብ ስለ ምን አትጨርሱም?
እያሉ በእስራኤል ልጆች ላይ
የተሾሙትን አለቆቹን ገረፉ።
5


ሕዝቡም
መከራ ያመጣችሁብን
እናንተ ናችሁ ብለው
ሙሴንና አሮንን
አማረሩ። ሙሴም
ወደ እግዚአብሔር
ፀለየና። ጌታ ሆይ፥
አንተም ሕዝብህን ከቶ
አላዳንኸውም አለ።
እግዚአብሔርም፡-እኔ
እግዚአብሔር ነኝ፥
ከግብፃውያንም ባርነት
አወጣችኋለሁ
ብሎ መለሰ።
6


እግዚአብሔርም
ሙሴንና አሮንን እንደገና
ወደ ፈርዖን ላካቸው።
ፈርዖንም፦ ተአምራትን
አሳዩኝ ሲላቸው፥አሮን
በትሩን በፈርዖንና
በባሮቹ ፊት ጣለ፥
እባብም ሆነች።
7


ፈርዖንም ጠቢባንንና
መተተኞችን ጠራ የግብፅም
ጠንቋዮች በአስማታቸው
እንዲሁ ደግሞ አደረጉ።
እያንዳንዳቸውም
በትራቸውን ጣሉ፥
እባቦችም ሆኑ የአሮን
በትር ግን በትራቸውን
ዋጠች።
8


በነገታው ሙሴና አሮን ፈርዖንን ወንዝ ዳር አገኙት። አሮንም በትሩንም አነሣ፥ በፈርዖንና በባሪያዎቹም ፊት የወንዙን ውኃ መታ የወንዙም ውኃ ሁሉ ተለውጠ ደም ሆነ። ዓሦች ሞቱ ወንዙም ገማ፥ ግብፃውያንም ከወንዙ ውኃ መጠጣት አልቻሉም።
9


ነገር ግን ፈርዖን ልቡን አደነደነ። ሕዝቡንም ለመልቀቅ እንቢ አለ።
10


ሙሴ ፈርዖንን “ሕዝቡን ልቀቅ” ብሎ እንደገና ተናገረው። እግዚአብሔር ሌላ መቅሰፍት ላከበት። ጓጉንቸሮችም ወጥተው ወደ ቤት፥ ወደ መኝታ ቤት፥ ወደ አልጋህ፥ ወደ ምድጆች፥ ወደ ቡሃቃዎችም ገቡ።
11


ፈርዖንም ጓጉንቸሮቹን እንዲያርቅልን ወደ እግዚአብሔር ጸልዩልኝ፤ ሕዝቡን እለቅቃለሁ አላቸው። ጓጉንቸሮቹ ሲወገዱ ፈርዖንም መልሶ ልቡን አደነደነ።
12


አሮንም እጁን ዘረጋ፥ በበትሩም የምድሩን ትቢያ መታው፥ በሰውና በእንስሳም ላይ ቅማል ሆነ። የፈርዖን ልብ ግን ደነደነ።
13


ቀጥሎም እግዚአብሔር የዝንብ መንጎች፤ ሰውንና ከብቶቹን የገደለ ብርቱ ቸነፈር፤በሰውና በእንስሳም ላይ ቍስል ላከባቸው። ፈርዖን ግን አሁንም ልቡን አደነደነ። ሕዝቡን አለቅም አለ።
14



ከዚያም አንበጣዎች
በአገሩ ሁሉ ላይ
ወጡ። የአገሪቱን
ቡቃያ ሁሉ በዛፉ
የነበረውን ፍሬ ሁሉ፣
ለምለም ነገር ዛፍም
የምድር ሣርም ሁሉ
በሉ።

15



ከዚያም ሙሴ
እጁን ወደ ሰማይ
ዘረጋ፥ በግብፅም
አገር ሁሉ ላይ ፅኑ
ጨለማ ሦስት ቀን
ሆነ። ይሁንና ፈርዖን
እስራኤላውያንን
ሊለቅቃቸው
አልፈቀደም።

16

እግዚአብሔርም
ሙሴን፦በግብፅ ላይ
ገና አንዲት መቅሰፍት
አመጣለሁ አለ።
ከፈርዖን በኵር
ጀምሮ ወፍጮ ፈጭ
እስከሆነችው እስከ
ባሪያይቱ በኵር
ድረስ፥ የከብቱም
በኵር ሁሉ ይሞታል
አለው። እንደዚያም
ሆነ እስራኤላውያን
የበራቸውን መቃን
በበግ ደም ስለቀቡት
በኩራቸው አልሞተም።



17



በሌሊትም በግብጽ
ምድር ታላቅ ለቅሶ
ሆነ። በእያንዳንዱ
ቤት ቢያንስ አንድ
ሰው ሞቷል።

18



ፈርዖንም ሙሴንና አሮንን
በሌሊት ጠርቶ፡- እናንተ
የእስራኤል ልጆች ተነሡ፥
ከሕዝቤ መካከል ውጡ ሂዱም፥
እንዳላችሁም እግዚአብሔርን
አገልግሉ አላቸው።

19



እግዚአብሔር ሙሴን “ይህ የፋሲካ
ምሽት የእግዚአብሔር መልዐክ የግብፅን
በኩር የገደለበት የእናንተን ግን
ያለፈበት ነውና አትርሱት” አለው።

20



ከ 430 ዓመታት የባርነት ቆይታ በኋላ
የእግዚአብሔር ሕዝቦች ነጻ ወጡ።
እግዚአብሔርም ቀን በደመና አምድ
ሌሊት ደግሞ በእሳት አምድ
መራቸው።

21



ፈርዖንም
እስራኤላውያንን
አልተዋቻውም።
እግዚአብሔርን
ረሳ። እንደገና
ልቡን አደነደነ።
ሰራዊቱንም
አሰልፎ
አሳደዳቸው።

22

ሙሴም ለሕዝቡ። “እግዚአብሔር ስለ እናንተ ይዋጋል”
አላቸው። ሙሴም በባሕሩ ላይ እጁን ዘረጋ።

23



ታላቅ ተዓምር ሆነ።
እግዚአብሔርም ሌሊቱን
ሁሉ ጽኑ የምሥራቅ
ነፋስ አምጥቶ ባሕሩን
አስወገደው፥ ባሕሩንም
አደረቀው፥ ውኃውም
ተከፈለ። ሕዝቡም
በሰላም ተሻገሩ።

24

ግብፃውያንም፥ የፈርዖን ፈረሶችና ሰረገሎች ፈረሰኞቹም ሁሉ፥
እያሳደዱ በኋላቸው ወደ ባሕር መካከል ገቡ። ውኃውም ተመልሶ
በኋላቸው ወደ ባሕር የገቡትን ሰረገሎችን ፈረሰኞችንም
የፈርዖንንም ሠራዊት ሁሉ ከደነ ከእነርሱም
አንድ ስንኳ አልቀረም። ፈርዖንም
እግዚአብሔር ታላቅ እንደሆነ አየ።



25

ደህና ሰንብት ፈርዖን!

ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል
በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

ዘጸአት ምዕ. 4-15

“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”
መዝሙረ ዳዊት 119:130

26




11 60



ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የሚያስተምረን ግሩም ስለሆነው አምላካችን እግዚአብሔር እኛን በመፍጠሩ እሱን እንድታውቀው ነው።

እግዚአብሔር “ኃጢአት” ብሎ የሚጠራውን ክፉ ነገር እንዳደረግን ያውቀዋል። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው ነገር ግን እግዚአብሔር በጣም ስለወደደን አንዱንና ብቸኛው ልጁን ለቀራኒዮ መስቀል ሞት አሣልፎ በመሥጠት እንዲሞትና የኃጢአታችንን ዋጋ በእኛ ምትክ በመሞት እንዲከፍል አደረገው። ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ በምድር ላይ ቆይቶ ወደ ሠማይ ወደ አባቱ አረገ! ያላመንን እኛም በኢየሱስ አዳኝት ብናምን እና ኃጢአታችንን ይቅር እንዲል ብለምነው ይቅር ይለናል። ደግሞም ያደርገዋል። እሱም በእኛ ውስጥ ይኖራል፤ እኛም በእርሱ ውስጥ ለዘላለም እንኖራለን አሜን።

ይህ እውነት እንደሆነ ካመናችሁ፣ እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተ አምላክ እንደሆንክ አምናለሁ ነገር ግን ለእኔ ኃጢአት ለመሞት ስትል ሰው ሆንህ አሁን ደግሞ ህያው ነህ። እባክህ ወደ ህይወቴ ግባ ኃጢአቴን ይቅር በል በዚህም አዲስ ህይወት አሁን ይኖረኛል አንድ ቀን ከአንተ ጋር ለዘልዓለም ለመኖር ወደ አንተ እመጣለሁ። ለአንተ እንድኖርና እንደ ልጅ እንድታዘዝልህ እርዳኝ። አሜን።

በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ከእግዚአብሄር ጋር ተነጋገር! የሐ. 3.16